ጎሕ ቤቶች ባንክ
GOH BETOCH BANK

## የጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ.
## የባለአክሲዮኖች 4 ኛ መደበኛ እና 2 ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ

በኢፌዲሪ ንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 366(1)፣ 367(1) እና 370 እንዲሁም በባንኩ የመመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 11.2.4 እና የመተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 8(1)፣8(3) መሠረት የጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ. የባለአክሲዮኖች 4ኛ መደበኛ እና 2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ህዳር 11 ቀን 2018 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡ 30 ጀምሮ በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ ይካሄዳል። በመሆኑም የተከበራችሁ የባንኩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንድትገኙ የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪዉን ያስተላልፋል።

**1. የባንኩ መረጃዎች**

1.1. የባንኩ ስም፡- ጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ.
1.2. የባንኩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ፡- አ.አ. ከተማ፣ ቦሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 2፣ የቤት ቁጥር አዲስ፤
ድረ ገጽ፣ https://www.gohbetbank.com/
1.3. የባንኩ የምዝገባ ቁጥር፡- MT/AA/3/0052524/2013
1.4. የባንኩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡- ብር 2,176,227,000.00
1.5. የባንኩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡- ብር 1,520,440,000.00

**2. የ4ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች**

2.1. የጉባኤውን አጀንዳ ማፅደቅ፣
2.2. የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮችን ማሳወቅና አዳዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበል፣
2.3. እ.ኤ.አ የ2024/2025 የዳይሬክተሮች ቦርድን አመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ፣
2.4. እ.ኤ.አ የ2024/2025 የውጭ ኦዲተሮችን አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዳመጥ፣
2.5. በተራ ቁጥር 2.3 ላይ በቀረበው የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ላይ መወያየትና መወሰን፣
2.6. በተራ ቁጥር 2.4 ላይ በቀረበው የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት ላይ መወያየትና መወሰን፣
2.7. እ.ኤ.አ የ2024/2025 የሂሳብ ዘመን የተጣራ ትርፍ አመዳደብ እና አከፋፈል ላይ መወያየትና ውሳኔ ማሳለፍ፣
2.8. የውጭ ኦዲተሮች የ2024/2025 እና የ2025/2026 አመታዊ የአገልግሎት ዋጋ ማሻሻያ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፣
2.9. የዳይሬክተሮች ቦርድ የ2024/2025 አመታዊ የሥራ ዋጋ እና የ2025/26 ወርሃዊ አበል መወሰን፣
2.10. በተሻሻለው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ የአሰራር ደንብ ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ።

**3. የ2ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች**

3.1. የጉባዔውን አጀንዳ ማፅደቅ
3.2. የባንኩን የመተዳደሪያ ደንብና የመመስረቻ ፅሑፍ በማዋሀድ የተሻሻለው የመመስረቻ ጽሑፍ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

**4. ማሳሳቢያ**

4.1. በጉባኤዉ ላይ መገኘት የማትችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ በተሰጠ የዉክልና ሰነድ (ተወካይ ዋናዉን እና ፎቶ ኮፒ እንዲሁም የተወካዩን ማንነት የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒ በመያዝ) ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በባንኩ ዋና መ/ቤት 2ኛ ፎቅ በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በባንኩ የተዘጋጀዉን የዉክልና ቅፅ ሞልታችሁ በመፈረም ተወካይ በመሾም በጉባኤው እንዲሳተፉ ማድረግ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን።
4.2. አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛዉም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ተወካይ ብቻ ነዉ። ሆኖም ሥራ ላይ ያለዉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ወይም የባንኩ ሠራተኛ የባለአክሲዮን ተወካይ ሆኖ ሊሾም የማይችል መሆኑን እናሳዉቃለን።
4.3. የባንኩን ረቂቅ የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሑፍ እና የተሻሻለ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ የአሰራር ደንብ ከባንኩ ድረገጽ https://www.gohbetbank.com/ ወይም የባንኩ ዋና መ/ቤት 2ኛ ፎቅ የአክሲዮን አስተዳደር ክፍል ማግኘት ይቻላል።
4.4. በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ አዋጅ ላይ በተደነገገው መሠረት ተገቢውን የባለአክሲዮኖች መረጃ ለማሟላት እንዲረዳ ባለአክሲዮኑ ወይም ተወካይ የባለአክሲዮኑን የዲጂታል መታወቂያ ካርድ (ፋይዳ) ኮፒ ይዘዉ እንዲቀርቡ እንጠይቃለን።
4.5. ለተጨማሪ መረጃ የባንኩ ዋና መ/ቤት 2ኛ ፎቅ የአክሲዮን አስተዳደር ክፍል በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር +251-116687252 በስራ ሰአት በመደወል መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

**የጎሕ ቤቶች ባንክ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ**